# ምዕራፍ አንድ

## ምክረታ

አወሊያ ገናና ምርጥ ተወዳዳሪ ያልነበራት በስሟም ሆነ በምግባሯ በዓለም አቀፍ መድረኮች ከፍ ብላ የምትጠራ ሀገርና ሕዝብን አገናኝ ድልድይ ነበረች። ነገር ግን በየዘመኑና በየምክንያቱ ብትር የሚበዛባት፤ ጉዞዋ ጠመዝማዛና ውጣ ወረድ የበዛበት፣ ወደቀች ሲሉ መነሳት ተነሳች ሲሉ መውደቅ እጣ ፈንታዋ ነበር። ያላትን ሃብት እንኳ በአግባቡ እንዳትጠቀም በቀጥታና በተዘዋዋሪ ሁኔታ እንቅፋት የበዛባት፤ እያላት እንደሌላት እንደዚህ በአረም እንደተከበበችዋ መርከብ ወደፊትም ወደኋላም እንዳትሄድ እግሯን ተተብትባ ታስራ ጉዞዋን ቀጥላለች። ለመሆኑ አወሊያ መች እና የት ጀመረች የሚል በጽሁፍ ተደገፈ የጊዜና የቦታ መረጃ በአጥጋቢ ሁኔታ ማግኘት ባይቻልም በሁለት መልክ (ገጽ) ያገኘሁትን መረጃዎች  የሰዎችንና የተበታተኑ  መረጃዎችን በማሰባበሰብ ለማየትና ለማቅረብ ሞክሪያሁ። በአንደኛው ገጽ እንደ ኢትዩጵያን አቆጣጠር በ1940ዎቹ በመርካቶ አካባቢ የጉዞ መነሻ እንደነበራት ሲነገር በሌላው ገጽ ደግሞ በ1950ዎች አጋማሽ በአንዋር መስጅድ መነሻ ማድረጓን የሚጠቅሱ አሉ። ሁለቱም ግን ሙሉ ሙሉ የአሁኑን ስያሜዋን ይዛ ከቀድሞ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ፊት ለፊት በሚገኘው ህንጻ በመከራየት መጀመርዋን ይስማማሉ።

## የአወሊያ አንዱገጽ

የመጀመሪያው መስራችና አሰተማሪ እንደሆኑ የሚነገርላቸው የመናዊው ኡስታዝ ዓሊ ይባላሉ። ት/ቤቱን ወደፊት ማዝለቅ ባለመቻላቸው በ1950ዎች ት/ቤቱን እንደዘጉት ይነገራል። በጊዜው የነበሩ አስር ሀብታም ዐረቦች የኡስታዝ ዓሊን ሥራ ፈትቶ መቀመጥ ልባቸውን ስለነካው ሊረዷቸው ተነሱ። 1500 ብር በማዋጣትም ት/ቤቱን መልሰው እንዲከፍቱ አበረታቷቸው። ኡስታዙም ሦስት ክፍሎችን ተከራይተው ትምህርት መስጠት ጀመሩ። በ1961 ዓ.ል አንዋር መስጅድ አጠገብ የሚገኝ ባለ አንድ ፎቅ ህንጻ ውስጥ ለሁለት መምህራን በወር ሃምሳ ብር እየከፈሉ ቀጥረው ማስተማር ጀመሩ።

በወቅቱ የተማሪዎቹ ወርሃዊ ክፍያ ከ10 እስከ 15 ብር ስለነበር ትምህርቱን የሚከታተሉት የሀብታም ዐረብ ልጆች ብቻ ነበሩ። የት/ቤቱ ሥርዓተ ትምህርትም ከግብዕና ከሊባኖስ የተቀዳና ቁርኣን፤ ተውሒድ፤ ፊቅህ፤ እንግሊዝኛና ሂሳብን የያዘ ሆኖ በዐረብኛ ቋንቋ የሚሰጥ ነበር።  ኡስታዝ ዓሊ በ1962 ዓ.ል ትምህርት ቤቱን ለኢትዮጵያዊው አቶ አህመድ ሁሴን በ3000 ብር በመሸጥ ወደ የመን አቀኑ። አቶ አህመድም የትምህርት ቤቱን ስያሜ ‹‹ከኡስታዝ ዓሊ መድረሳ›› ወደ ‹‹አወሊያ ትምህርት ቤት›› ለወጡት። በመቀጠልም የተማሪዎችን ወርሃዊ ክፍያ በመቀነስ ከ5-10ብር እንዲሆን ሲያደርጉ በአንጻሩ የመምህራኑን ደሞዝ ከፍ አድርገዋል።

ከመስከረም 1963 ዓ.ል ጀምሮም የትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ገጽታ እየተቀየረ መጣ። ከ1963-64 የኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ብዛትም 20 በመቶ ደረሰ። በ1965 ዓ.ል ደግሞ የኢትዮጵያዊያን ቁጥር ከዐረብ ተማሪዎች መብለጥ ቻለ።

በዚህ መካካል ግን ትምህርት ቤቱ የገንዘብ አቅሙ ስላነሰ አቶ አህመድ ወደ መካ ለሐጅ በተጓዙበት ወቅት የሙስሊም ወርልድ ሊግን (ራቢጠተል ዓለመል ኢስላሚን) እርዳታ ጠይቀው ሳይሳካላቸው ተመለሱ።

በ1966 ዓ.ል የሊጉ ልዑካን ኢትዮጵያን ሊጎበኙ ተዘዋውረው ከተመለከቷቸው ቦታዎች አንዱ የአወሊያ ትምህርት ቤት ነበር። የሊጉ መሪዎች ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላም ትምህርት ቤቱን ሊረዳ የሚችልበትን መንገድ ቀየሱ። ከ1968 ጀምሮም በሳውዲ ዐረቢያ ኤምባሲ በኩል ድጋፍ ማግኘት ጀመረ።

አቶ አህመድ የትምህርት ቤቱን የወደፊት ጉዞ ለማጠናከር እንዲረዳቸው በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀም ጀመረ። በዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ በ1972 ትምህርት ቤቱ የትምህርት ሚኒስቴርን እውቅና አግኝቶ የግል የህዝብ ትምህርት ቤት ሆነ።

ከ1975 ጀምሮም የሙስሊም ወርልድ ሊግ የትምህርት ቤቱን ሙሉ ወጪ መሸፈን ጀመረ። በመስከረም 1984 ትምህርት ቤቱ በመሰፋፋት 9ኛ ክፍል ተከፈተ። በ1985 ደግሞ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር ጀመረ። በ1975 የግል ትምህርት ቤቶችን ብሄራዊ የማድረግ አዋጅ ሲወጣ አወሊያም የህዝብ ትምህርት ቤት ሆነ። በኋላ ላይ ኮሚቴው ‹‹ትምህርት ቤቱ የሃይማኖትና የአካዳሚክ ትምህርት እንዲያስተምር ሆኖ ስለተቋቋመ በሚሽን ትምህርት ቤትነት ይመዝገብ›› ሲል ለትምህርት ሚኒስቴር አመለከተ። ጥያቄያቸው በትምህርት ሚኒስቴር ተቀባይነት አገኘ።

በወርልድ ሙስሊም ሊግና በትምህርት ሚኒስቴር መካከል እ.ኤ.አ ማርች 31 ቀን 1985 በተደረገው ስምምነት መሰረት በእንግሊዝኛ ከተጻፈው ውል ሁለቱን ልጥቀስ ፡-

ARTICLE I No.1 *The school hitherit known as the "Awolia public Elementery and secondary school" shall be renamed as "Awolia Muslim School"*

ከላይ እንደተጠቀሰው *‹‹አወሊያ የህዝብ ት/ቤት›› የነበረው ‹‹አወሊያ ሙሰሊም ትምህርት ቤት›› በመባል* ስሙ መቀየሩን ተስማምተዋል።


ሌላውና ወሳኙ የስምምነት አንቀጽ ይህኛው ነው።

ARTICLE I Sub Article 3 "*The School may provide Islamic Education and Arabic Launguage along with the National Curriculum."*

*"ይህ አንቀጽ እንደሚገልጸው ትምህርት ቤቱ ከብሄራዊ ስርዓተ ትምህርቱ ጋር የኢስላማዊ ትምህርትና የዐረብኛ ቋንቋን ጨምሮ መስጠት ይችላል"* በሚል የኢትዮጵያ መንግስት በትምህርት ሚኒስቴሩ አማካኝነት መፍቀዱን ያሳያል።

## የዓለም አቀፉ ሙስሊም ሊግና የት/ት ሚ/ር ስምምነት

ት/ቤቱ ከ1976-85 እኤአ ባሉት ዓመታት 410 ተማሪዎች ለብሄራዊ ፈተና ሲያስቀምጥ ከነዚህ ውስጥ 87 በመቶ የሚሆኑት ፈተናውን ማለፍ ችለዋል። ትምህርት ቤቱ ካፈራቸው ተማሪዎች ውስጥም በርካቶች በ1971 እኤአ የተቋቋመውን የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች ክበብ በመቀላቀል ኃይለ ሥላሴን ለማስወገድ በተደረገው ትግል ውስጥ ተሳትፈዋል።



ከ2006 እ.ኤ.አ በኋላ ግን ትምህርት ቤቱ ራሱን መቻል አቅቶት እየተንገዳገደ መቀጠሉን እና በአጠቃላይ ከጊዜ ወደጊዜ የትምህርት ጥራቱም እየወረደ መሄዱን አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ መምህራን ሳይቀር ይናገራሉ።

## የ አ ወ ሊ ያ ጉ ዞ ሌ ላ ው ገ ጽ

68ኛ ዓመቱን የያዘው አወሊያ ት/ቤት በ1944 ዓ.ል ነበር የተቋቋመው። የትምህርት ቤትን አስፈላጊነት የተረዳው የመናዊው ኡስታዝ ዓሊ በትምህርት ሥራ ላይ የመሳተፍ ፍላጎት አድሮበት በወቅቱ ሙስሊሞች በሥፋት ይኖሩበታል ተብሎ በሚታሰብበት መርካቶ ምዕራብ ሆቴል አካባቢ ቀዳማዊ ወይም



‹‹አወሊያ›› ብሎ ት/ቤት ከፈተ። ይህ የየመን ተወላጅ በአዲስ አበባ የየመናውያንን መኖር፣ በመርካቶ የሐደራዎች መብዛትና በቅርብ ርቀት የአንዋር መስጅድ መኖር ለቦታ መረጣው ስልታዊ እንደነበር ማወቅ ይቻላል። ራሱን ጨምሮ ሌሎች መምህራንንም አክሎ እያስተማረ ሳለ በወቅቱ የመን ውስጥ በተካሄደው መፈንቅለ መንግሥት የአብደላ ሰላሕን መንግሥት ሥልጣን መጨበጡን ሲሰማ ‹‹ለኔ የሚሻለኝ የማምንበትን መንግሥት መደገፍ ነው›› በሚል ትምህርት ቤቱን ሸጦ ወደ የመን ያመራል።

ት/ቤቱን የገዛው ከየመኒው ጋ አብሮ ሲያስተምር የነበረው ምስጉኑ መምህር አህመድ ሁሴን ነበር። አህመድ ሁሴን ከፊል የዐረብ ዝርያ ያለው በጣም ጎበዝ የነበረ ሰው ነው። መጀመርያ የአወሊያ ዳይሬክተር ቀጥሎ የሳዑዲ ኤምባሲ ሠራተኛ ኋላ የጃሊያ ዳይሬክተር የነበረ ሰውም ነበር። በግርርው ሂደት ሸህ ዐብዱልሓፊዝ የተባሉ ሐደራም ነበሩ። ሸህ ዐብዱልሐፊዝ ጎበዝ የኾጥ አስተማሪ እንደነበሩ ይነገራል። ሁለቱ ሰዎች በጋራ በመሆን ከመርካቶ በመውጣት የቀድሞው ማስታወቂያ ሚኒስቴር ፊት ለፊት ያለውን ቤት ከአንድ ባለሃብት ይከራያሉ። የቤቱ ባለቤቱ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ እንደነበሩ ይነገራል።


ሁለቱ ተከራይተው እያስተማሩ ሳለ አጼ ኃይለሥላሴ በንጉሥ ፈይሰል ዘመን ሳውዲን ለመጎብኘት ወደ ሳውዲ ዐረቢያ ይሄዳሉ። ንጉሱ ሲመለሱም ሰዋፍ የሚባሉ ሸኽ የዐረቦችን ትምህርት ማለትም የዐረብኛ የትምህርት ሂደትን ለማስተማር በመፈለግ አብሯቸው ይመጣል። ንጉሱም አዲስ አበባ ውስጥ የፈለግከው ቦታ መርጠህ አስተምር ይሏቸዋል። በወቅቱ የፈለግከውን የተባሉት ከዑመር ሰመተር፣ ከአወሊያ፣ ከአሁኑ አፍሪካ አንድነት ት/ቤት (ት/ቤቱ ያኔ በቀደመው ዘመን የሙስሊም ት/ቤት ነበር) መሳለሚያ አካባቢ ካለው ዛሬ ዳግማዊ ብርሃን ከሚባለው ት/ቤት እንዲሁም መሐል መርካቶ ሳጥን ተራ አካባቢ የነበረ ሱመያ ት/ቤት መካከል ነበር እንዲመርጡ የተፈቀደላቸው።

ሸህ ሰዋፍ አወሊያን መረጡ። መምረጥ ብቻም ሳይሆን ሸህ አህመድ ሁሴን ከየመኒው የገዛበትን ብር ከፍሎ ወደ ሳውዲ ወስዶ በትምህርት ካሪኩለምና የትምህርት አሰጣጥ ስልት ተነጋግረው ዳግመኛ የት/ቤቱ ዳይሬክተር አድርገው ሹመው ላኩት። አህመድ ሁሴን ሥራውን ተረክቦ እስከ ደርግ መምጫ ሲያስተምሩ ቆዩ። ደርግ ሲመጣ በከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጅ ቤቱን ወርሶ የሕዝብ ት/ቤት አደረገው።

## በደርግ ዘመን

ት/ቤቱን ተረክበው እያስተማሩ ሳለ የደርግ ኮለኔል የነበሩት ኮለኔል ጧሂር የአስኮውን ቦታ ለማስገኘት ጥረት አድርገው ተፈቀደ። ደርግ በወቅቱ ሰዎች ብዙም የማይኖሩበትን አካባቢ ከአስፋልቱ እስከ ተራራው ጥግ ድረስ ቦታውን ሰጣቸው። አካባቢው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነበር። ከቦታው ሰፊነት የተነሳ አጥር ማሳጠሪያ ገንዘብ ማግኘት አልተቻለም ነበር።

አወሊያ በየጊዜው የተለያዩ ፈተናዎችን አልፋ ዛሬ ለዳግም ሕዳሴ በቅታለች። በዚህ ት/ቤት ታሪክ አሻራቸውን ያሳረፉ በርካታ አስተዳደሮች ነበሩ። የሀጅ ሻሚል ውልሰቦ አስተዋጽኦ ቀላል አልነበረም። ሐጂ ሻሚል ውልሰቦ ለአወልያ ሕልውና ብዙ ታግለዋል። አስኮ ለሚገኘው አወሊያ ት/ቤት አጥር ማሳጠርያ ሸህ ኢብኑ ባዝ 50 ሺህ ብር ልከው እንደነበር፣ ሌላው አህለል ኸይር ሐጂ ቱሬ የተወሰኑ ክፍሎችን እንዳሠሩ፣ ኩዌቶችም የመማርያ ክፍሎችን እንዳሠሩና ሳዑዲዎችም ድጋፉን እያደረጉ የማስተማሩ ሂደት እስከ ኢህአዴግ መምጫ ድረስ መቀጠሉን በወቅቱ የነበሩት ሰዎች ያወሳሉ።


ሀጅ ሻሚል ወልሰቦ


ሸህ ኢብኑባዝ


ሀጂ ቱሬ

## በኢህአዴግ ዘመን

ኢህአዴግ አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ በግንቦት 1983 ዓ.ል ቅሬታ ሰሚ ኮሚሽን ያቋቁማል። በየቦታው የተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ አወሊያም ይገባል። በአወሊያ ሸህ አብደላ ኢድሪስ፣ አቶ ኤልያስ፣ አቶ መሐመድ ሸህ አብዱሰላም የተባሉ ታላላቅ ሰዎች ይመረጣሉ። በወቅቱ ዳይሬክተሩ አቶ ኢድሪስ የተባሉ ሰው ሲሆኑ አስተዳደሩ ደግሞ አቶ ሻሚል ውልሰቦ ነበሩ። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ለሳዑዲ ኤምባሲ ‹‹ት/ቤቱ ስሙ የሕዝብ ት/ቤት ነው ገንዘቡን የሚሰጠው ደግሞ ራቢጠተል ኢስላሚያ ነው። እንዲህ በተራራቀ መንገድ መሥራቱ ተገቢ ስላልሆነ ለምን የሙስሊም ሚሲዮን ት/ቤት አይባልም›› ብለው ያመለክታሉ።

አምባሳደሩ ‹‹እውነታችሁን ነው›› ብሎ የአስተዳደር ኮሚቴውን ጠርቶ ‹‹እናንተ ነጋዴዎች ናችሁ ስለ ት/ቤት እውቀት የላችሁም እናንተ ለቅቃችሁ የሙስሊም ሚሲዮን ት/ቤት ቢሆን ምን ይመስላችኋል?›› በማለት ያማክሯቸዋል። እነሱም ‹‹ይሁን›› ብለው ይስማማሉ። በወቅቱ የትምህርት ሚኒስቴር

ሚኒስትር አቶ ኢብሳ ጉተማ ነበሩ። አቶ ኢብሳ ነገሩን አድምጠው ለማስፈጸም ሳይችሉ ይቀራሉ። ኮሚቴው ዘለግ ያለ ጊዜ ምላሹን ቢጠብቁም ሲያጡ በአቶ መሐመድ ሸህ አብዱና በጓደኛው የገነት ዘውዴ ወንድም አማካይነት የወቅቱ የትምህርት ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር የነበሩት ወ/ሮ ገነት ዘውዴ ጋ በመሄድ ዝርዝሩን ያስረዳሉ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ሚኒስትሩ ኢብሳ ጉተማ ከሀገር ወጥተው በዚያው ይቀራሉ። ወ/ሮ ገነት ዘውዴ ደግሞ በሚኒስትርነት ማዕረግ ላይ ይሾማሉ። ኮሚቴዎቹ እንደነገሩን ‹‹እኛም ሄደን በይ አስፈጽሚልን የምታውቂው ነገር ነው አልናት። በየጊዜው ማድረግ የሚገባንን ስትነግረን እኛም ስናደርግ ብዙ ጊዜ ፈጅብን።›› ይላሉ።

አወሊያ ዘመናዊ ትምህርት፣ የአረብኛ ቋንቋና የዲን ትምህርት በጥራት ይሰጥ የነበረበት፣ በጤናው ዘርፍ ሙስሊምና ሙስሊም ላልሆኑት በርካታ የሀገራችን ሕዝቦች አገልግሎት ይሰጥ የነበረና የ1977 ዓ.ል የሀገራችን ድርቅ ተከትሎ በርካታ የእርዳታ ሥራዎችን ቦታው ድረስ በመሄድ የረዳ፣ በሺ የሚቆጠሩ በድርቁ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናት አዲስ አበባና ወሊሶ በማምጣት በማሳደግ በርካቶች ራሳቸውንና ሀገራቸውን ይጠቅሙ ዘንድ ለቁም ነገር ያበቃ ተቋም ነበር።

ከላይ በቀረቡት የመርከቢቷ አወሊያ አመሰራረት ታሪክ የምንረዳው በቅድሚያ በየመናዊው አሊ እንደተመሰረተች ቀጥሎም ኢትዮጵያዊው አህመድ ሁሴን ፤ በተለያዩ ኮሚቴዎች በመቀጠልም መረከቡን በሂደት ወርልድ ሙስሊም ሊግ ከዛም ዓለም አቀፉ ኢስላማዊ እርዳታ ድርጅት በቅብብሎሽ ማስተዳደራቸውን የግል፤ የሕዝብና ሚሽነሪ ት/ቤት በመባል አገልግሎቷን በማስፋት ዛሬ ላይ መድረሷን ያሳያል።

## አወሊያ ዛሬስ?

ዛሬ ምንም እንኳ አወሊያ በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ሰብስቦ ቢያስተምርም በተለይም ከሰኔ 2003 ዓ.ል መጀሊሱ ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ በገቢም በአገልግሎትም ቁልቁል እየወረደ ሲሆን ይባስ ብሎ በኮቪድ 19 ሰበብ ለመምህራኑ ደሞዝ መክፈል አቅቶት ክብርና ዝናው ኮስሶ በሀፍረት አንገቱን ደፍቷል። ሆስፒታሉ የተሟላ መሳርያ ባለማግኘቱ በበቂ አገልግሎት እየሰጠ አይደለም፣ ኮሌጁ በበጀት እጥረት ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አልቻለም፣ ቀድሞ ከአዲስ አበባ ት/ቤቶች በትምህርት ጥራትና ውጤት የላቀ ደረጃ ላይ የነበረው፣ ዛሬ ከግማሽ በላይ የሁለተኛ ደረጃ ማጠቃለያ የወሰዱ ተማሪዎች ውጤት በማጣት እቤታቸው እንዲቀመጡ ተገደዋል፣ በደሞዝ ማነስና በአግባቡ አለመክፈል ምክንያት በርካታ መምሕራን ት/ቤቱን ለቀው በመሄድ ችግሩ እንዲደራረብ ምክንያት ሆኗል። የደሞዝ ክፍያው የወቅቱን ገበያ ያማከለ ባለመሆኑ በአዳዲስና ጎበዝ መምህራን ተመራጭ እንዳይሆን አድርጎታል።

እነዚህ ችግሮች ግን መምህራን ወላጆችንና የቀድሞ ተማሪዎች ማኅበር እንዲሁም ባለድርሻ አካሉን እጁን አጣጥፎ እንዲቀመጥ አላደረገውም። በየጊዜው የተለያዩ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ ጥሯል። የት/ቤቱን አስተዳደር ከመቀየር አንስቶ በወላጆች ላይ የክፍያ ጭማሪ በማድረግ የገንዘብ እጥረቱን ለመሸፈን ተሞክሯል። በመጨረሻ ነገሮች ወደ መስመር እንዲገቡም ት/ቤቱን ከአስተዳዳሪው ከመጅሊስ አመራር እንዲወጣ አድርጎ በቦርድ እንዲዋቀር ተደርጓል። ይህ ሂደት እየተከናወነ ባለበት ወቅታዊው ዓለም አቀፍ ችግር በት/ቤቱ የለውጥ ሂደት ላይ ጋሬጣ በመፍጠር ጭራሽ የኢኮኖሚ ማንሰራራቱን ድባቅ እንዲመታ አድርጓል።

በአሁኑ ወቅት ት/ቤቱ በገቢ ራሱን እንዲችል የትምህርት ጥራቱን በ85 በመቶ ለማሻሻል፤ የጤና አገልግሎት አሰጣጡን በ75 በመቶ እንዲያሳድግ ጥረት እየተደረገ ነው። የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ እየተነደፈለት ይገኛል። በተለያዩ ጊዜያት ተቆርሰው የተወሰዱ የድርጅቱ ይዞታዎችን የማስመለስ እና በካርታው እንዲካተቱ በማድረግ ማኔጀመንቱ ከፍተኛ አስተዋጸ አድርጓል። ተቋርጠው የነበሩ የሕጻናት ማሳደግያና የቁርአን ሒፍዝ ማዕከላት አገልግሎት ለማስቀጠል እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ከፍተኛ የሆነ የገጽታ ግንባታ በመሥራት ት/ቤቱን ወደቀድሞ ዝናውና ክብሩ ለመመለስ ሌት ተቀን እየተሰራ ይገኛል።

ከ2002ዓ.ል እስከ 2003ዓ.ል መጨረሻ በወላጅ፤ተማሪ፤መምህር ህብረት (ወተመህ) እና በአይ አር ኦ ማኔጀመንት መካከል ከፍተኛ የሆነ የእርስበርስ ትግል የነበረበት ወቅት ነበር።

በወቅቱ የአይ አር ኦ ሙዲሮች ከሀገር የወጡበትና በማኔጀመንት ድርጅቱ የሚመራበት ወቅት ነበር።


ወተመህ ትምህርት ቤቱን ማስተዳደር ያለብን እኛ ነን፤ ከፍተኛ የአሰራርና የገንዘብ ብክነት ይታያል ፤ አይ አር ኦ ከግቢ ውጪ ቢሮ ተከራይቶ በውጪ ነው መርዳት ያለበት የሚል አቋም ይዞ የሚንቀሳቀስ ሲሆን ለዚህም የትምህርት ቢሮ መመሪያና ደንብን እንደማስረጃ ያቀርቡ ነበር። ከዚህም አያይዘው አስተዳደራዊና የፋይናስ ግልጽነት ጉድለት መኖሩን በመጥቀስ በከፍተኛ ይሞግታሉ። በወቅቱ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ትምህርት ቤቶችን እንዲያስተዳድር የጻፈላቸውን ደብዳቤ በማስረጃነት ያቀርባሉ።

በአይ አር ኦ ማኔጅመንት በኩል ደግሞ አወሊያን ማስተዳደሩ ኃላፊነት ከወርልድ ሙስሊም ሊግ በመረከብ ‹‹እያስተዳደርኩት ያለሁት እኔ ነኝ ስለዚህ አጠቃላዩን የአወሊያ ጉዳይ እኔን ነው የሚመለከት›› በማለት የትምህርት ሚኒስቴርንና የሊጉን ስምምነት በማሰረጃነት ያቀርባሉ። የሁለቱ ወገን ክርክር ከፍ እያለ በመሄድ አንዱ ሌላውን በመክሰስ እስከ ጠቅላይ ሚኒስቴርና ኢህአዴግ ጽ/ቤት እንዲሁም አሉ የሚባሉ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶችና አካላት ጋር እንዲደርስ ተደርጓል።

በዚህ ወቅት ለአራት ወራት ያህል የመምህራንና ሠረተኞች ደመወዝ ያልተከፈለበት የመማር ማስተማሩም ይሁን ሌሎች አገልግሎቶች እየተዳከሙ የመጡበት ወቅት ነበር። ውጥረቱ እያየለ ሲሄድም ለነበረው መንግስት ምቹ ሁኔታ የፈጠረ በመሆኑ ሁለቱም አካላት በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በመጥራት ከዚህ በኋላ እርዳታ ድርጅቱን መጂሊሱ እንዲረከበው በመንግስት መወሰኑን በመግለጽ ሁለቱም አካል ወደቤታቸው አንዲገቡ የሚያመላክት ውሳኔ ተገለጸላቸው። በወቅቱ የመንግስት አካሄድ የገባቸው ማኔጀመንት አባላቱ ወሳኔውን ተቀብለው ሲወጡ የወተመህ አካላት ግን ለተወሰነ ጊዜም ቢሆንም ከመጅሊስ አመራር ጋር ለመከራከር ቢሞክሩም እንደማያስኬድ ሲያውቁት ወሳኔውን ለመቀበል ተገደዱ። የሁለቱ አካላት ወዝግብም በዚሁ ተጠናቀቀ።

ዓለም አቀፍ እውቅና የነበራት አወሊያ በየጊዜው ከምታስተናግደው መከራ የአሁኑ ከምትሸከመው በላይ ሆኖባታል።

በ1940ዎቹ ጥቂት ሕጻናትን ቁርአን በማስተማር ሥራውን አሃዱ ያለው የኡስታዝ አሊ መድረሳ የዛሬዋ አወሊያ (የዓለም አቀፉ ኢስላማዊ እርዳታ ድርጅት የኢትዮጵያ ቢሮ) ከ60 ዓመታት በላይ በዘለቀው ጉዞው አስቸጋሪ መሰናክሎችን አልፎ አሁን የሚገኝበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ‹‹በኢትዮጵያ ብቸኛው እና ትልቁ የሳውዲ አረብያ እርዳታ ድርጅት›› የሚል ማዕረግ ተሰጥቶት ነበር።








**ዓለም አቀፉ ኢስላማዊ እርዳታ ድርጅት(IIRO)  ፌደራል መጅሊስ**

## የ ባ ለ ቤ ት ነ ት ለ ውጥና ሕዝ ባ ዊ ተ ቃ ው ሞ ው

**ተቋመ· ወደ እርዳታ ድርጅትነት ከተሸጋገረ በኋላ የፋይናስ አቅመ· ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረ ቢሆንም በተለያየ ወቅት በተከሰቱ የአሰራር ግድፈቶች የተቋመ· ሕልውና አደጋ ላይ ወድቆ ታይቷል። የተቋመን ህልውና ካናጉ ፈተናዎች ሁሉ የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ በነሀሴ 19/2002ዓ.ል ለእርዳታ ድርጅቱ የጻፈው ደብዳቤ የከፋው ነበር።**












ድርጅቱ (IIRO) በቀጥታ የወርልድ ሙስሊም ሊግ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት አካዳሚክ ትምህርትና ኢስላማዊ ትምህርት ጎን ለጎን መስጠት እንደሚችል ስምምነት መኖሩ እየታወቀ የሃይማኖትን ትምህርትና የልማት ሥራን ቀላቅለሃል በሚል ሰበብ ፈቃድህ ተሰርዟል መባሉ ተገቢ አልነበረም። ድርጅቱ ተቃውሞውን ቢያቀርብም ሰሚም አላገኘም።

በሌላ በኩል በተለይ ጳጉሜ 1/1998 ዓ.ል በጻፉት ደብዳቤ በተረጂው ስም የተሰበሰበው ገንዘብ፤ ሃብትና ንብረት ለብክነት የተጋለጠ ስለመሰለን በቃህ የሚል አሳፋሪ ደብዳቤም በወቅቱ በነበሩት የትምህርት ሚኒስቴር ዶ/ኤታ ስመኝ ውቤ ፊርማ ለትምህርት ሚኒስቴር የተጻፈ ደብዳቤም ነበረበት።

በመጨረሻም ዋናው የመንግስት ዓላማ የድርጅቱን ፈቃድ ነጥቆ ወደ መጣበት ሀገር ማሰናበት ነበረና፣ ፈቃድህ ተሰርዟል የሚል ደብዳቤ ጻፈ።


የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲም ሰኔ13/2003ዓ.ም ጠቅላይ ም/ቤቱን ተረክብ የሚል ደብዳቤ ጻፈለት።





ለሀገርና ለህዝብ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረው የሳዑዲው ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅት በመንግስት በኩል በአይነ ቁራኛ ይታይ የነበረ ሲሆን ፈቃድህን አድስ ስትባል ማደስ አልቻልክም በሚል ውስጠ ወይራ መልዕክት መስከረም 10/2003 ዓ.ል ከበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ በተጻፈ ደብዳቤ አወሊያን ከሳዑዲ ዐረብያ የእርዳታ ድርጅት መዳፍ ፈልቅቆ ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት (መጅሊስ) እንዲሰጥ አድርጓል።

በዚሁ መሰረት መጅሊሱ አወሊያን ለመረከብ መዘጋጀቱን በመግለጽ የሚረከቡትን አባላት ዝርዝር በሚከተለው ደብዳቤ ለኤጀንሲው ላከ፡





የሀብት እና እዳ አጣሪ ኮሚቴ ቢዋቀርም እርዳታ ድርጅቱ የነበረበት የመንግስት እዳ ብር 320.43 (ሶስት መቶ ሃያ ብር ከ43 ሳንቲም) ያልተከፈለ የኢንተርኔት እዳ ብቻ ሲሆን በአጠቃላይ በተለያዩ የባንክ አካውንት ብር 3,276,434.81 አስቀምጦ የወጣ ንጹህ ድርጅት በመሆኑ የሰራተኛን እዳ ከፍሎ ቀሪ ብር 677,661.73 በትርፍነት ጥሎ የወጣ በመሆኑ መንግስት በምንም መልኩ ለመወንጀል የሚያስችል ምክንያት ሊያገኝ ባለመቻሉ ፈቃዱን ብቻ በመሰረዝ መጅሊሱ እንዲረከበው አደረገ፡፡

በነዚህ ተወካዮች አማካኝነት በተደረገው ርክክብም አወሊያ ላትመለስ ወደ መጅሊሱ ተጠቃለለች፡፡ ኤጀንሲው ከጻፋቸው ደብዳቤዎች ውስጥ ለመጅሊሱ ከጻፋቸው ጥሩ ደብዳቤ አካዳሚክና የሃይማኖት ትምህርቱን በሊጉ ስምምነት መሰረት መስጠት እንደሚችል ነበር፡፡ አይ.አር.ኦን. ግን ወንጅሎ ፈቃዱን የሰረዘው የሊጉን ስምምነት ወደጎን በማድረግ ከአካዳሚክ ትምህርቱ ጋር የሃይማኖት ትምህርት በመስጠቱ ነው በሚል ነበር፡፡

ይህ ከታች የተጻፈው ደብዳቤ መጅሊሱ በሊጉ ስምምነት መሰረት ሃይማኖታዊ ትምህርት ጨምሮ መስጠት እንደሚችል በመግለጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ጥያቄው ግን መንግስት ለሙስሊሙ አስቦ ወይስ ያኔ ራሱ መንግስት ለኢትዮጵያውን ሙስሊሞች የሚመች ሃይማኖት ከሊባኖስ Impoert በማድረግ ለመጥመቅና የአወሊያን ካሪኩለም በመቀየር ሊያስተምሩን በማሰብ እንደነበር ስንቶቻችን ገብቶን ይሆን? ለነገሩ ቢገባንማ ነው እንቢ ለሃይማኖቴ በማለት ውስጠ ወይራው ጉዞ በቁርጥ ቀን ልጆቿ እንዲመክን የተደረገው፡፡ ለማንኛውም ራሳቸው በጻፉት ስምምነት አወሊያ ብቸኛዋ የአካዳሚክና ኢስላማዊ ትምህርት አጣምራ የምትሰጥ ት/ቤት አድርጓታል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Charities and societies Agency

ቁጥር ፈ.ኢ.ር/ድ.ኤ.ማ/ —५०२३/
Ref.
ቀን 20 ሮ.ኤ 20፲፫
Date

ለ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

**ጉዳዩ፦ የአጠቃላይ ትምህርት ቤት ጉዳይን ይመለከታል!**

የአጠቃላይ ትምህርት ቤት ከተቋቋመ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ የሕዝብ ትምህርት ቤት ሆኖ በሂደት አጋጥሞት በነበረው የፋይናንስ ችግር ምክንያት በትምህርት ሚኒስቴር እና በአለም ሙስሊም ሴኘ መካከል በተፈረመ ውል ሴኘ ትምህርት ቤቱን እንዲደገፍ ስምምነት ተፈፅሞ እንደነበር ይታወሳል። ነገር ግን ኋላ በተካሄደው ማጣራት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በማያውቀውና መጀመሪያ ተፈርሞ የነበረውን ስምምነት በጣም ሁኔታ ኢንተርናሽናል ኢስላሚክ ሪሊፍ ኦርጋናይዜሽን የተባለ የውጪ በጎ አድራጎት ድርጅት ጣልቃ ገብቶ በሂደት የፈጠራቸው በርካታ ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው አጠቃላይ ትምህርት ቤትንም ሲደግፍ እና በትምህርት ቤቱ ግቢም ሆነ ሴሎች ቦታዎች ላይ የተለያዩ ግንባታዎችን አካሂዷል ድርጅቶችንም አቋቁሞ እንደነበር ለማረጋገጥ ተችሏል።

ይሁንና ኢንተርናሽናል ኢስላሚክ ሪሊፍ ኦርጋናይዜሽን በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111(2) መሠረት በዘጎ አደራጭት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ጽሃፍ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ባለማሟላቱ ሳይመዘገብ ቀርቷል።

ስለሆነም ድርጅቱ ጽሃፍ ባለመመዝገቡ ምክንያት በኤጀንሲው በኩል "ሞኖሮ" የቸለከ ሲሆን ድርጅቱ በኤጀንሲው ውሳኔ ላይ ስዘን አደራጭት ድርጅቶችና ማኅበራት ቦርድ አቅርቦ ቦርዱ ጉዳዮን በማርገር ከተመለከተው በኋላ ኤጀንሲ የሰጠው ውሳኔን አጽንቷል።

የቦርዱን ውሳኔ መሠረት በማደረግ የድርጅቱ ሀብትና አዳውን አጣርቶ በአዋጁ መሠረት ቀመሳሰይ ዓላማ ላለው ድርጅት ለማስተላለፍ እንዲቻል በድርጅቱ በኩል የሥራ መሪዎቹ ወይም ተወካይ እንዲገኝ በርካታ ጊዜ ጥሪቶች ቢደረጉም ድርጅቱ ሳይቀርብ ሳይገለጽ ቀርቷል።

በመሆኑም የትምህርቱ ሂደት መቀጠል ስላለበት ቀደም ሲል IIRO ሲሰጥ የነበረውን አገልግሎት በመስጠት ከአለም ሙስሊም ሴኘ ጋር ተደርጉ በነበረው ውል መሠረት ኃላፊነቱን ሊሸከም የሚችል አካል ለማፈላለግ በኤጀንሲውም ሆነ ጉዳዩን እንዲከታተል በተቋቋመው ኮሚቴ በኩል ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል። የአጠቃላይ ትምህርት ቤት በአንደ በኩል በመንግስት የትምህርት ካሪኩለም መሠረት የትምህርት ሥራውን የሚያካሄድ ከመሆኑም በላይ በተጨማሪ መሠረታዊ የኃይማኖት ትምህርቶችንና አጠቃላ ቋንቋ ትምህርትም እንደሚሰጥ ለመረዳት ችለናል። በሴላ በኩል ደግሞ በትምህርት ቤቱ ግቢ ሕይማኖታዊ ተቋማት፣ የህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት የጤና ተቋም እና ሌሎች ግንባታዎችም በመካሄዳቸው እነዚህ ዘርፈ ብዙ የሆኑ አገልግሎቶችን ባሉበት ሁኔታ አስጠብቆ ሊያስቀጥል የሚችል ድርጅት የኢትዮጵያ አስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ብቻ መሆኑን በመረዳት ቀደም ሲል IIRO ሲያከናውናቸው የነበሩ ተቻቻራትና ቢሥሩ የነበሩ ተቋማት በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ አስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት እንዲተላለፉ በኤጀንሲው በኩል ተወስኗል። ስለሆነም ድርጅቱን ወክሎ ሥራዎቹን ሲመራ የነበረው ማኔጅመንት ኮሚቴ ርክክቡን እንዲፈፅም ውሣኔው ደርሷቸው የርክክቡ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

ስለሆነም አጠቃላ ትምህርት ቤትን አስመልክቶ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአለም ሙስሊም ሴኘ መካከል በተረገው ስምምነት መሠረት በአሁኑ ጊዜ የአለም ሙስሊም ሴኘን ተክቶ የኢትዮጵያ አስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የሚሠራ በመሆኑ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩል ይኸው ታውቆ ትምህርት ቤቱንና የትምህርት ሥራውን በተመለከተ የበኩሉን አስፈላጊ ክትትል እንዲያደርግ በማክበር እናስታውቃለን።

ከሠላምታ ጋር

ዋልዛዥ
- ለ ፈዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
- ለ ኢትዮጵያ አስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት
  አዲስ አበባ


ስልክ Tel. +0111373041
ፋክስ FAX +0111367811
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia